# የበዓላትና የአጽዋማት ቀኖና

በኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ አወዛጋቢና አከራካሪ የሆነው በቤተ ክርስቲያንም በኩል ሰፋ ያለ ማብራሪያ ለመስጠት አስቸጋሪ መስሎ የሚታየው የበዓላትና የአጽዋማት ጉዳይ ነው። ስለዚህ ስለ በዓላትና አጽዋማት ባጭሩ እንገልጣለን።

ሀ/ በዓላት ፦ በዓላት በልማድ የሚከበሩ ወይም ቁጭ ብሎ መዋልን የለመደ የወደደ ሰነፍ የፈጠረባቸው አይደሉም፤ ምንጫቸው ወይም የት መጣቸው ሃይማኖት ነው። በብሉይ ኪዳን ብዙ በዓላት ነበሩ፤ ከእነዚህ ቀዳሚዉ "ቀዳም ሰንበት" ናት። የዚህች ዕለት ክብር ከዐሥሩ ቃላት አራት በአንዱ ታዟል። "እግዚአብሔር አምላክህን ሰንበት አክብር" ተብሎ አይሁድ ዕለት ሰንበትን እንዲያከብሩ የታዘዙት፣ የእግዚአብሔር አሐድ እስከ ዓርብ ሲፈጥር ሰንብቶ በዚህች ዕለት ስላረፈ(ሥራ) ስላልሠራበት ነው። ስለ ቀዳም ሰንበት ክብር የአይሁድ ሊቃውንት ብዙ ዓይነት አተረጓጎም ነበራቸው። አክብር" የሚለውን ቃል ለእግዚአብሔር እንዲስማማ አድርገው ለመተርጎም ያላዩት መዝገብ ቃላት የለም። ካህናቱም ሆነ ሕዝቡ በዚህች በዕለት ሰንበት ሥር መማስ፣ ቅጠል መበጠስ ይቅርና የዘረጉትንም አያጥፉም፤ ያጠፉትንም አይዘረጉም፤ የበጉትን አይከፍቱም፤ የከፈቱትን አይዘጉም ነበር። ዜና አይሁድን የጻፈው ራሱም አይሁዳዊ የሆነ ዮሴፍ ወልደ ኮራዮን፦ "አይሁድ በዕለት ሰንበት ወደ ሽንት ቤት እንኳ አይሔዱም ነበር" ይላል። ከዚህም ጋር ቤት ቢቃጠል፣ ሰው ቢሞት ጦር ቢመጣ፣ በዕለተ ሰንበት ከሆነ መንቀሳቀስ ክልክል ነው። ለምሳሌ በመቃብያን ታሪክ እንደሚታወቀው 36ሺህ አይሁዳውያን በወራሪ ጦር በአንድ ቀን ያለቁት በዚህች በዕለተ ሰንበት ነበር። በ1966 ዓ.ም በፈረንጆች 1973 ዩም ኪፑር ግብጻውያን ያጠቋቸው በበዓሉ ምክንያት ተዘልለው ሳሉ ነው። አይሁድ ብዙ በዓላት አሏቸው። የበዓላቸውም ሕግ ማንኛውንም ሥራ ከመሥራት መጠንድ ነው። በሌላው ዓለም ያሉ አረማውያን ደግሞ የራሳቸው በዓላትና የአከባበር ሥርዓቶች አሏቸው። አማልክቶቻቸው ብዙ እንደመሆናቸው መጠን ብዙ በዓላትና የተለያዩ የአከባበር ሥርአቶች አሏቸው። ለምሳሌ፦ 12 አማልክት የነበራቸው ጽርዓውያን በነዚያው ልክ በዓላት ነበሯቸው። አከባበራቸውም እንደ አምልኮታቸው ከፍርሃት የመነጨ እንጂ መጽሐፋዊ ወይም ምሥጢራዊ ስላልሆነ ስለ ሥርዓቱ ብዙ አያስቡበትም። በሚኖሩበት አካባቢ አንድ ለውጥ ሲያዩ ብቻ ቶሎ ብሎ መሥዋዕት ያቀርቡ ነበር። "ነፋስ ሲነፍስ የነፋስ አምላክ(ኤዎሎስ) ተቆጥቶ ነው። የፀሐይ ሙቀት ሲያይል የፀሐይ አምላክ (አጵሎን) ተቆጥቶ ነው። ባሕር ስትታወክ የባሕር አምላክ (ፖሲዶን) ተቆጥቶ ነው በማለት ካህናቱ ጣዖቱ በዓል ያዘጋጁ መሥዋዕት ይሠዉ ነበር። የበዓል አከባበራቸው ሥራ የማይከለክል ነበር የቆመውን ነበር። እነዚህ፦ ማለት አይሁድና አረማውያን ወደ ክርስትና በገቡ ጊዜ የቆየውን ልማዳቸውን ለመተው አስቸጋሪ ነገር ገጥሟቸው ነበር።

የመጀመሪያዎቹ የወንጌል መምህራን ሐዋርያት ይህ ልማድ መሰናክል እንዳይሆን ሁሉንም እንዳመሉ ተቀበሏቸው። ከአይሁድ ወደ ክርስትና የተመለሱት የክርስቶስን አዳኝነት አምነው ከተቀበሉና ክርስቲያን ከሆኑ በኋላ ግን ቅዳሜንም፣ እሑድንም ያከብራሉ። ግዝረትና የመሳሰለውም የብሉይ ኪዳን ትውፊት ከቤተ አይሁድ በተመለሱት ክርስትያኖች ዘንድ እስከ አሁን ይሠራበታል። ከአራማዊነት የተመለሱት ደግሞ እንደዚሁ የክርስቶስን አዳኝነት አምነው ከተቀበሉና ክርስቲያን ከሆኑ በኋላ ልማደ አረማውያንን አልተውም። የቅዳሜን በዓልነት አያውቁም፤ ግዝረት የላቸውም።

ሊቃውንቱና መምህራኑ የሕዝቡን የረጅም ዘመን ፍቅረ ጣዖት ለማስተው ስላቃታቸው በጣዖታቱ ተሰይሞ ይከበር የነበረውን ሁሉ በቅዱሳን ስም እየለወጡ ያከብሩታል። ለምሳሌ፦ በጣዖታዊነት በነበሩበት ጊዜ "ፖሲዶን" የሚባለው ጣዖት የባሕር አምላክ ነበር፤ በክርስትና ዘመናቸው ግን ሊቃውንቱ "ኒኮላዎስ" የሚባለውን ቅዱስ የባሕር ጠባቂ ብለው በዮሙቱ ያከብሩታል። የመርከበኞች በዓል ነው። "አሬስ" ወይም "ማርስ" የጦር አምላክ ተብሎ ሲመለክ የኖረ ጣዖት ነው። በሱ ምትክ ዛሬ ቅዱስ ጊዮርጊስን የወታደሮች ጠባቂ ብለው በዮሙቱ ያከብሩታል።

በጠቅላላው አመራውያን ለእያንዳንዱ ድርጊት (ፍጥረት) አምላክ መድበውለት ስለነበር ዛሬ በቤተ ክርስቲያናቸው የሚከበሩት ቅዱሳን መላእክት ጻድቃን ሰማዕታት ሁሉ የአንዳንድ ነገር ጠባቂዎች እየተባሉ ተሰይመዋል። በአረማውያን የበዓል አከባበር "ኢታንሥእ እደዊከ ወእገሪከ" የሚል ትእዛዝ ስላልነበረ አሁንም ከአረማዊነት የተመለሱት ክርስቲያኖች በዓል የሚያከብሩት ሥራ ፈትቶ ተቀምጦ በመዋል አይደለም። ለምሳሌ፦ በዓሉ የቅዱስ ጊዮርጊስ እንደሆነ የጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባለበት ቅዳሴ ይቀደሳል፤ የሰበካው ሕዝብ ይልቁንም በስሙ የተሰየሙት ምእመናን ያስቀድሳሉ፤ ቅዱስ ቁርባንንም ይቀበላሉ፤ ከጸሎተ ቅዳሴው ፍጻሜ በኋላ በጊዮርጊስ ስም የተሰየመው ሁሉ ከቤታቸው ተቀምጠው ወዳጅ ዘመድ የሆነ ሁሉ "የክርሞ ሰው" ይበልህ እያለ የሚያመጣላቸውን ስጦታ በየይነቱ ሲቀበሉ ይውላሉ።

የመንግሥት በዓላት "ብሔራዊና ሃይማኖታዊ" በዓላት፡ እንደ ልደት፣ ጥምቀት፣ ትንሣኤና ፍልሰታ ኪዳነ ምሕረት በሚከበሩበት ጊዜ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከመዘጋታቸው በቀር እያንዳንዱ ግለሰብ በየቤቱ የግል ሥራውን ቢሠራ ለራሱ ከልደከመ በቀር ከጎረቤትም ሐሜት አያስከትልበትም። እሱም ለራሱ በዓል እንደሻረ አድርጎ አይቆጥረውም። እንደ አርእስቱ ስለ በዓላት አጀማመርና የተለያዩ ሥርዓቶች እንሥተናል። የሀገራችንስ የበዓል አከባበር እንዴት ነው?

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የበዓላት ቀኖና የራሱ የሆነ መልክ አለው። ከሁሉ በፊት ቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሜንና እሑድን እንደ አንድ ቀን አድርጋ (አስተካክላ) ታከብራለች። የቅዳሜ መከበር በብሉይ ኪዳን የታዘዘ ሲሆን፣ እሑድ ደግሞ ጌታ ከሙታን ተለይቶ ስለተነሣበት "የጌታ ቀን" ተብሎ በሐዲስ ኪዳን የከበረች ናት(ራእ 1 ቁጥር 10)።

በነዚህ ሁለት ቀኖች ምንም እንኳ ቤተ ክርስቲያናችን የክርስቲያኖች አከባበር እንደ አይሁድ ሰውን የሚጫን እንዳይሆን ብታስተምርም "ኢይደልዎሙ ለክርስቲያን ከመ ያጽርዑ ተግባሮ በዕለተ ሰንበት ከመ አይሁድ አላ ይትገበሩ ከመ ክርስቲያን ወኢትትዐቀቡ ሰንበተ ከመ አይሁድ" (ፍት 19) "ወዕረፍትሰ አኮ በሰኪብ ከመ ዘሐመ በደዌ አላ በትጋሀ መዓልተ ወሌሊተ ከመ ንኩን ፍቁራኒሁ ለዛቲ ዕለት" (ቅዳ፤ አትና) ሕዝቡ ከብሉይ ኪዳን በወረሰው ትውፊት መሠረት በዕለተ ሰንበት ብቻ ሳይሆን በሌሎችም በዓላት ማናቸውንም ሥራ ቢሆን አይሠራም። ሌላው ቀርቶ ቅዳሜና እሑድ የተቀዳ ውሃ የተወቀጠ ቡና የማይጠጡ ወንዝ የማይሻገሩ ክርስቲያኖች አሉ። በሌሎቹም በዓላት እንደ ሰንበት አይጾምም እንጂ፤ ሥር ማማስ፣ ቅጠል መበጠስ፣ መጽሐፍ መጻፍ፣ መደጎስ፣ ልብስ ማጠብ ሁሉ በዓል እንደመሻር ይቆጠራል። ይህ ሁሉ ከሕዝቡ ልማድ ጋር የተያያዘ ስለሆነ እንጂ በቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሠረት የተደነገገ አይደለም፤ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት የጌታ በዓላት ዘጠኝ ናቸው። እነዚህም "ዐበይት በዓላት" (ታላቅ በዓላት) ይባላሉ።

<u>1ኛ ብሥራት</u> ፦ መጋቢት 29 ቀን ነው፤ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለድንግል ማርያም የአምላክን ከርሷ መወለድ ያበሠረበት ቀን ነው። በመንጸፈ ደይን ለነበረው የሰው ዘር ታላቅ የምሥራች ነውና የምሥራች ቀን (ብሥራት) ተብሏል።

<u>2ኛ ልደት</u> ፦ በትንቢተ ነቢያት የተነገረለት የሰውን ልጆች ጥንተ ተፈጥሮ የፈጠረ የእግዚአብሔር ልጅ አሁን ደግሞ በሐዲስ ተፈጥሮ ለመፍጠር ማለትም፦ ሰውን ለማዳን ሰው ሆኖ የተወለደበት ዕለት ነው። ልደት በየዓመቱ የሚከበረው ታኅሣሥ 29 ቀን ነው። በዘመነ ዮሐንስ ግን (የሉቃስ ጳጉሜን ስድስት ስለሆነች) ልደት ታኅሣሥ 28 ቀን ይሆናል። ይህም የተጀመረው በዓፄ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ነው ይባላል። የልደት በዓል ከጾም ጋር የተያያዘ ስለሆነ ገሃድ የለውም፤ የማይጾሙ ሰዎች ግን ዋዜማውን ብቻ ገሃድ ብለው ይጾሙታል። በዘመነ ዮሐንስ ልደት ሐሙስ በ28 ቀን ቢውል 29 ዓርብ ይጾማል። ልደት በ28 ማክሰኞ ቢውል 29 ረቡዕ ይጾማል። ሁለቱንም ቀን ልደት ማለት ግን ጥሩ አይደለም። ከዚያስ ያንኑ 29ኙን መያዙ ይሻላል። በዚህ የቀን ስሌት ብዙ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ሲጣሉበት ኖረዋል። ለወደፊቱም ይህን ለማስተካከል የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ሙሉ መብት አለው።

<u>3ኛ ጥምቀት</u> ፦ ክርስቶስ በተወለደ በ30 ዓመቱ የማዳን ሥራውን በጥምቀቱ ጀምሯል። ጌታ የተጠመቀው በፈለገ ዮርዳኖስ ነው፤ ያጠመቀውም ዮሐንስ ወልደ ዘካርያስ ነው። በተጠመቀም ጊዜ አብ በደመና ሆኖ የምወደው የምወልደው ልጄ ይህ ነው ብሎ መሰከረለታል፤ መንፈስ ቅዱስም በጸዓዳ ርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ተቀምጧል። ይህ በዓል በሚከበርበት ጊዜ በዋዜማው ታቦታቱ ከየቤተ ክርስቲያናቸው ወጥተው በወንዝ ዳር(በሰው ሠራሽ የውሃ ግድብም ቢሆን) በዳስ በድንኳን ያድራሉ። ሌሊት ስብሐተ እግዚአብሔር ሲደርስ አድሮ ሥርዓተ ቅዳሴውም ይፈጸማል። ሲነጋ በወንዙ ዳር (በግድቡ) ጸሎተ አኮቴት ተደርሶ አራቱም ወንጌላት ከተነበቡ በኋላ ወሃው ተባርኮ ለተሰበሰበው ሕዝብ ይረጫል። የጠበሉን መረጨት አይተው በቀድሞ ዘመን ወደ ሀገራችን መጥተው የነበሩ ኢየሱሳውያን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ትጠምቃለች ብለው አቃለው ጽፈዋል።ነገር ግን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ይህን የምትፈጽመው ጌታችን ለኛ ብሎ ያየውን ትሕትና ለመመስከር ለምእመናን የጌታን በረከተ ጥምቀት ለማሳተፍ እንጂ የተጠመቁትን ምእመናን እየመላለሰች በየዓመቱ አታጠምቅም። ጥምቀት አሐቲ መሆኗን ታውቃለችና። እርግጥ ያልተጠመቁ አረማውያንና ሌሎችም የጥምቀት በዓል በሚከበርበት ጊዜ እየመጡ በክርስቶስ አምነው ይጠመቃሉ። ጥምቀት የሚከበረው በየዓመቱ ጥር 11 ቀን ነው። ጥምቀት ረቡዕ ቢውል ገሀዱ ማክሰኞ፤ ዓርብ ቢውል ገሃዱ ኀሙስ ለውጥ ሆኖ ይጦማል። ጥምቀት የሚውልባቸው ዐርብና ረቡዕ አይጦሙምና። በበዓለ ጥምቀት የታቦታቱ ወደ ወንዝ መውረድ ጌታችን በእደ ዮሐንስ ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ የመሔዱ ምሳሌ ነው።

4ኛ ደብረ ታቦር ፦ ጌታ በማስተማር በነበረበት ጊዜ በደብረ ታቦር ላይ ብርሃን መለኮቱን ክብረ መንግሥቱን የገለጠበት ዕለት ነው። ይህ በዓል በየዓመቱ ነሐሴ 13 ቀን ይከበራል። ይህ በዓል በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በተለይም በምእመናን ዘንድ የተለየ ስም አለው በምእመናን ዘንድ፦ ቡሄ ይባላል። ቡሄ ማለት (መላጣ ገላጣ) ማለት ነው። በሀገራችን ክረምቱ አልፎ ተዋግዶ የብርሃን ወገግታ የሚታየው በዚሁ በዓል አካባቢ ስለሆነ "ቡሄ" የሚለው ስያሜ ሳይሆን አይቀርም። "ድርጊቱ በተፈጸመበት በፍልስጥኤም ግን የደመና መልክ የማይታይበት ፍጹም የበጋ ወራት ነው" በሀገራችን ሕፃናቱ ይህ በዓል ከመድረሱ በፊት ቀደም አድርገው ጅራፍ ሲገምዱና ሲያሞሙ(ሲያናኙ) ይሰነብታሉ እናቶችም ለዚህ በዓል የሚሆን ዳቦ ለመጋገር (የሚከበረው በዳቦ ነውና) ስንዴያቸውን ሲያጥቡ ሲፈትጉ ይሰነብታሉ። በዓሉ አንድ ነገ ሲሆን አንድ ዛሬ በዋዜማው (ነሐሴ 12) የመፈር ሕፃናት በየቤቱ እየዞሩ ቡሄ በሉ፤ ቡሄ መጣ ያ መላጣ፤ ቅቤ ቀቡት እንዳይነጣ፤ እዚህ ላይ ቡሄ ያሉት ዳቦውን ነው። በዚህ ጊዜ እናቶች ካዘጋጁት ዳቦ እያነሱ ይሰጧቸዋል። ሕጻናቱ ዳቧቸውን እየገመጡ ሲጋረፉ ይውላሉ። ለግርፊያው ተምሳሌት ባይገኝለትም፣ የጅራፍ መምጮ የድምፅ መለኮት፤ ጅራፍ ሲጮህ ማስደንገጡ የሐዋርያትን (የጴጥሮስን፣ የያዕቆብንና፣ የዮሐንስን) በድምፀ መለኮት መደንገጣቸውንና መውደቃቸውን ያስታውሳል። አንዳንድ ተበሊዎች የቡሄ ዕለት ማታ ችቦ ያበራሉ። በደብረ ታቦር ለታየው ብርሃን መለኮት ምሳሌ ነው። በዚያውም ላይ በኢትዮጵያችን የዓት ክረምት ዋዜማ ስለሆነ ቡሄን ብርሃን ቢሉት ይስማማዋል። ዋቡሄ ዕለት ለዘመድ ላዝማድ ለእያንዳንዱ በተሰብ በልጆቹ ልክ ዳቦ ይሰጣል። በተጨማሪም ለክርስትና ልጅ ለሰጡት ልጅ ለአማችና ለምራት፣ የቅርብ ዕውቂያ ላለውም ሁሉ የቡሄ ዳቦ ይሰጣል። በተማሪ ቤት ደግሞ ደብረ ታቦር የተማሪዎች በዓል ነው። ተማሪዎች ቀደም አድርገው( ስለ ደብረ ታቦር) እያሉ እሀሉን ጌሾውን ብቅሉን ይለምናሉ፤ ሕዝቡም ባህሉን ስለሚያውቅ በገፍ ይሰጣቸዋል። የደብረ ታቦር ዕለት ጠላውን ጠምቀው ቆሎውን ቆልተው ዳቦውን ጋግረው ሲያስቀድሱ የመጡትን ምእመናን ሁሉ ከቅዳሴ በኋላ ይጋብዛሉ። ይህ እስካሁን በትምህርት ቤቶች የሚሠራበት ነባር ትውፊት ነው።

5ኛ ሆሣዕና ፦ ከትንሣኤ አንድ ሳምንት ቀድሞ በሚውለው እሑድ የሚከበር ነው። ታሪኩ በወንጌል ተመዝግቧል። በዓሉን በዚህ ዕለት እንዲሆን የወሰኑት ግን ሊቃውንት ናቸው። ሆሣዕና ማለት መድኃኒት ማለት ነው። በዚያች ዕለት ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ሆሣዕና እያሉ ስላመሰገኑት ዕለቱ በጌታ ስም ተጠርቷል። አንዳንዶች ክርስቲያኖች ደግሞ ሆሣዕናም ይላሉ። "የዐበርት እሑድም ይሉታል" ዐበርት እየተባረከ ለሕዝብ ይታደላል ሕዝቡም ዐበርቱን እየተቀበለ እንደ መስቀል አድርጎ እየሠራ በየቤቱ ይሰቅለዋል። እያንዳንዱም እንደ ጣት ቀለበት አድርጎ እየሠራ በጣቱ ይሰከዋል። ከቅዳሴ በኋላ በቤተ ክርስቲያን በአራቱም ማዕዘናት አራቱ ወንጌላት ይነበባሉ። ከሆሣዕና ጀምሮ እስከ ትንሣኤ ያሉት ዕለታት የዓመቱ ፍጻ መታሰቢያ (ሰሙነ ሕማማት) ስለሆኑ ጸሎተ ፍትሐት፣ ጸሎተ አስተብርዮ አይፈጸምም። ጸሎተ ፍትሐትና ጸሎተ አስተብርዮ የሚደረግ በዚሁ የሆሣዕና በዓል ዕለት ነው። በአክሱምና በሌሎችም አንዳንድ ቦታዎች ታሪኩን እንዳለ ለመግለጥ አህያ ጭነው በዚያ ላይ ሰው እያስቀመጡ ሥርዓተ ዑደት ይፈጸማል።

6ኛ ስቅለት ፦ የስቅለት በዓል ለዓለም ቤዛ ሲሆን መድኃኔዓለም የተሰቀለበት ዕለት ነው። የስቅለት በዓል ብዙ ዘርፍ አለው ከላይ እንደ ተገለጠው ከሆሣዕና ጀምረው ያሉት ዕለታት የዓመቱ ፍጻ መታሰቢያ ናቸው። በነዚህ ቀኖች ውስጥ ብዙ አዝማደ መባልዕት አይበሉም። ስግደት ይሰገዳል የጌታን መከራ ሞት የሚያስታውሱ ምንባባት ከቅዱስ መጻሕፍትና ከድርሳናት ሲነበቡ ይሰነብታሉ። ኅሙስ ጸሎተ ኅሙስ ይባላል። ጌታ በፍጹም ትህትና የደቀ መዛሙርትን እግር ያጠበበት ዕለት ነው። በዚህ ዕለት ቄሱ ውኃውን በብርት አድርጎ በጌታ አምሳል የምእመናንን እግር ይጥባል። ጸሎተ ቅዳሴው ከተፈጸመ በኋላ ምእመናን ወደ ቤታቸው ሔደው ዳቦና ጉልባን ይበላሉ። ለትንሣኤ የተዘጋጀው ጠላ የሚቀመሰው የዚያ ዕለት ነው። በነጋው የስቅለት ዐርብ የስቅለቱ መታሰቢያ አኅበር ተሠርቶ ስቅለቱ ነክ የሆኑ ምንባባት ሲነበቡና ሲሰገድ ይዋላል ሠርክ ሲሆን እያንዳንዱ ምእመን ወደ ቄሱ እየቀረበ በሰሙነ ሕማማት ውስጥ የሠራውንም ኃጢአት ይናዘዛል ቄሱም በወይራ ቅጠል እየጠበጠበ ተጨማሪ ቀን ሊሰግደው ከዋለው ሌላ ስግደት ይሰጠዋል። ጥብጣቢው የተግሣጽ ምሳሌ ነው። ዐሥራ ሁለት ሰዓት ሲሆን ሠርሆተ ሕዝብ ይሆናል። በቤተ ክርስቲያኖቻችን ልማድ አመቤታችን ያዕቆብንና ዮሐንስ የጌታን ትንሣኤ ሳናይ እህል ውኃ አንቀምስም ብለው እስከ ትንሣኤ ቆይተዋል ይባላል። በሀገራችንም ዛሬ እንኳ እንኳ ብዙ ሰዎች ኅሙስ ማታ የቀመሱ እሁድ የትንሣኤ ዕለት ብቻ ነው እህል ውኃ የሚሉት። ያልተቻላቸው ግን ዓርብ ማታ ትንሽ ቀምሰው እስከ ትንሣኤ ይሰነብታሉ። የሁለት ቀን ማክፈሉ እንኳ ቢከብድ ቅዳሜን ማክፈል ጥሩ ልማድ ነው። ቅዳሴው በመንፈቀ ሌሊት ስለሆነ በልቶ ማስቀደስ በልቶ መቁረብ እንዳይሆን።

7ተኛ ትንሣኤ፦ የትንሣኤ በዓል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን በመስቀል ተሰቅሎ በሞተ በኋላ ተቀበረ በሦስተኛውም ቀን መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል ከሙታን ተለይቶ የተነሣበት ዕለት ትንሣኤ ትባላለች። ትንሣኤ በዓል በቤተ ክርስቲያናችን ከሌሎች በዓላት ሁሉ በጣም በደመቀ አኳኋን ይከበራል የመንፈሳዊ ተመስጦ አለበት። ከአምሳ አራት ቀን የጾም ጉዞ በኋላ

የምትመጣ ስለሆነች ትንሣኤን ሁሉም ይናፍቃታል። ይልቁንም በአክፍሎት የሰንበቱ ሁሉ ዕረፍት ሥጋን ለማግኘት ትንሣኤን በናፍቆት ይጠባበቋታል። ቅዳሜ ማታ ለእሁድ አጥቢያ ሕፃኑ ሽማግሌው ወጣቱ ባለቤቱ በየሰበካ ቤተ ክርስቲያናቸው ይሰበሰባሉ። ሥርዓተ ጸሎት ይጀመራል። ለትንሣኤ በዓል በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተመዘገበው ጸዋትው ከተፈጸመ በኋላ በመንፈቀ ሌሊት ጸሎተ ቅዳሴ ይጀመራል። ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ሥርሀተ ሕገብ ይሆናል። የትንሣኤ ማዕድ ፦ በዕድ ዘመድ፣ ወዳጅ፣ ጠላት የማይለይበት የጋራ ማዕድ ነው። የትንሣኤ ዕለት ምንም ቢሆን ያለው በልቶ ያጣው ጦም አያድርም በከተማ እንጀ እንጀ በበዓገር እያንዳንዱ ምእመን የተቻላቸውን ያህል ተማሪ እየጠሩ የትንሣኤን ማዕድ አብሮ ይመገባል። በትንሣኤ ሳምንት በደብዳቤ በስልክም የሚሰጠው ሰላምታ፣ "እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ" ነው። መላሹም "እንኳን አብሮ አደረሰን" ይላል። (ጽርአውያን ከትንሣኤ እስከ ዕርገት አርባው ቀን ሰላምታ የሚሰጣጡት ፦ "ክርስቶስ ተንሥአ" ሲል አንዱ መላሹ ፦ "በአውነቱ ተንሥአ" ይላል። ከሕሙድ ጀምሮ እስከ ዳግም ትንሣኤ ያሉት ዕለታት እንደ አንድ ቀን ነው የሚቆጠሩት፣ መዝሙሩም ጸሎቱም አይለወጥም። ምዕራባውያን ከትንሣኤ ይልቅ ልደትን በደመቀ አኳኋን ይከበራሉ። ይኸውም ስለ ሁለት ምክንያት ነው። አንዱ ያው እንደ ክርስትያኖች ሁሉ ክርስቶስ የተወለደበትን ዕለት ለማክበር ነው። ሌላው ምክንያት ደግሞ ሳምንት ስለሆነ ተደራራቢ በዓል አድርገው ነው። በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ግን የበዓላት ሁሉ ቢሆን የክርስቶስ አምላክነት በይበልጥ የተገለጠው በትንሣኤው ስለ ሆነ ከልደት አብልጠው ያከብሩታል።

8ተኛ ዕርገት፦ ጌታ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ አርባ ቀን ለሐዋርያት እየተገለጠ ታይቷቸዋል። ትምህርትም አስተምሯቸዋል። በተነሣ በአርባኛው ቀን ቀደም አድርጎ እንደነገራቸው ለሐዋርያት አሁንም የመንፈስ ቅዱስን መምጣት ነግሮ ወደ ሰማይ የወጣበት ቀን ነው። ይህ በዓል በቤተ ክርስቲያን በጸሎት በማሕሌት ይከበራል። በሕዝቡ ዘንድ ግን መሰናዶ የለውም።

9ኛ ጰራቅሊጦስ ፦ ጌታ ባረገ ባሥረኛው በተነሣ በሃምሳኛው ቀን ለሐዋርያት በነገራቸው የተስፋ ቃል መሠረት መንፈስ ቅዱስን ላከላቸው። በዓሉ ጰራቅሊጦስ ባለው "ጰንጠቆስጤ" የሚል ይገኛል። ጰንጠቆስጤ ቃሉ የግሪክ ነው። "ፔንቴኮንቴ" "ፔንዲ ኮስቲ" አምስ አምሳኛ ማለት ነው። በብሉያትና በሐዲሳት በሌሎች መጻሕፍት ሁሉ ከዕብራይስጥና ከጽርእ ሳይለወጡ የገቡ ብዙ ጥሬ ቃላት አሉ። "ለምሳሌ፦ ኬፋ፣ ፋሲካ፣ ሊሲዮ፣ ላማ፣ ሰበቅታኒ" ከዕብራይስጥ "ጰንጠቆስጤ፣ ጰራቅሊጦስ፣ ጴጥሮስ፣ ክርስቶስ፣ ትብዔራ" ከጽርእ የተወረሱ ጥሬ ቃላት ናቸው። ጰራቅሊጦስ ማለት በጎን የሚቆም የሚረዳ የሚያጽናና ማለት ነው። ይህ በዓል በብሉይ ኪዳን የአዝመራ በዓል ነበር (በዓለ ሰዊት) እሥራኤል የነፃነት በዓላቸውን ከሚያከብሩት ከበዓለ ፋሲካ (በዓለ ፍሥሕ) ጀምረው አምሳውን ቀን በዓል አድርገው ይሰነብታሉ። በአምሳኛዪቱ ቀን በዓለ ሰዊትን(የአዝመራ በዓላቸውን) ያከብራሉ። በሀገራቸው ከመጋቢት እስከ ግንቦት ያለው ወቅት በሀገራችን ከመስከረም እስከ ህዳር እንዳለው የአዝመራ ወራት (የጸደይ ወራት) ነውና የአዝመራ በዓላቸውን የሚያከብሩበት በኦሪት ዘሌዋውያን ገበሬ ከዘራው ሁሉ በየደንቱ እሸቱን ቆርጦ ተሸክሞ ወደ ምኩራብ ይመጣል፣ በቤተ መቅደስ የሚያገለግለው ካህን ተቀብሎ ባርኮ ጸልዮ፣ የሚጠበሰው እየተጠበሰ የሚታሸው እየታሸ በማህበር አንድነት ይባላል። ይህም "ቀዳምያት ይባላል" የመጀመሪያው ማለት ነው። ከማንኛውም በረከት የመጀመሪያ እግዚአብሔር ፊት መቅረብ ለእግዚአብሔር መስጠት እንዳለበት ታዟልና። በዓለ ፋሲካን ለማክበር ከዝርወት ተሰብስበው የሰነበቱ አይሁድ ሁሉ ወደየመጡበት የሚመለሱት ይህን በዓለ ሰዊትን ከከበሩ በኋላ ነው። ይህን ሁሉ የገለጥነው በጽርሐ ጽዮን መንፈስ ቅዱስን ለሐዋርያት በተሰጠበት ዕለት የነበረው ሊታረሳችን መገናኛ እንዲሆን ነው። ከዝርወት የተሰበሰቡና በዚያውም የሚኖሩ አይሁድ አብዛኛውን ጊዜ በዓል የሚያከብሩ በደብረ ጽዮን ነው። ደብረ ጽዮን ጥንትም የዳዊት ከተማ ነበረች፣ የዳዊት መቃብርም በደብረ ጽዮን ነው፣ ይመጣል ብለው የሚጠብቁት መሲሕም በደብረ ጽዮን ይነግሣል ነው የሚሉት። እንግዲህ በዚች በደብረ ጽዮን በዓለ ሰዊትን ለማክበር ተሰብስበው እንዳሉ ሐዋርያት ደግሞ በዚሁ በደብረ ጽዮን በማርቆስ እናት በማርያም ቤት ውስጥ ተሰብስበው ነበር።

ጌታ ባረገ ባሥረኛው ቀን ጧት መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት ተሰጠ ጌታ የነገራቸው የተስፋ ቃል ሁሉ ተፈጸመ። ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው የሞቱና የትንሣኤው ምስክሮች ሆኑ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በነሱ ላይ ሲያድር ለቤተ ክርስቲያን ገፅ አዲስ ምዕራፍ ተከፈተ። ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዳለው ፦ "መንፈስ ቅዱስ ባይወርድላት ኖሮ የቤተ ክርስቲያን ሕልውና ከስምና ቀጭጮ ይቀር ነበር ስለዚህም በሚገባ እንጋገር ይህች ዕለት የቤተ ክርስቲያን የልደት ቀን ትባላለች" ይላል። ብዙ ሊቃውንት ይህችን ዕለት የበዓላት ሁሉ እመቤት ይሏታል። የጰራቅሊጦስ በዓል በክርስቲያን ዓለም ሁሉ ከትንሣኤው ቀጥሎ (በቤተ ክርስቲያን) የሚፈጸመው የጰራቅሊጦስ ዕለት ነው።

ዘጠኙ ዐበይት በዓላትና የት መጣቸው የአከባበራቸው ሥነ ሥርዓት ከዚህ በላይ እንዳየነው ነው። ከነዚህ ውስጥ ሆሣዕና፣ ስቅለት፣ ትንሣኤ፣ ዕርገትና ጰራቅሊጦስ በዓላት ዐዋድያት ስለሆኑ በቀን አቆጣጠር መባቻ

ሐመርን ተከትለው ወደ ላይ ታች ይላሉ። ዕለታቸው ግን አይፋለስም። ሆሣዕና፣ ትንሣኤ፣ ጰራቅሊጦስ እሑድን፤ ስቅለትን ዐርብን፤ ዕርገት ሐሙስን አይለቅም። ሌሎችም ፅንሰ ልደት ደብረ ታቦር ጥምቀት ግን ዐዋድያት አይደሉም፣ ዕለታቸው ግን የተፋለሰ ነው።

### ከዘጠኙ ዐበይት በዓላት ሌላ ዘጠኝ ንኡሳት በዓላት አሉ። እነሱም

1. መስቀል
2. ስብከት
3. ብርሃን
4. ኖላዊ
5. ግዝረት
6. ልደተ ስምዖን
7. ቃና ዘገሊላ
8. ደብረ ዘይት
9. የመጋቢት መስቀል(መጋቢት 10)

<u>ሀ/ የመስቀል በዓል</u> የሚከበረው መስከረም 17 ቀን ነው። ይህም በዓል በክርስትያን ዓለም ሁሉ ይከበራል። ታሪኩም በመጠኑ እንሆ ጌታ በመስቀል ላይ ሙቶ ከተነሣ በኋላ ሕሙማን መስቀሉን እየዳሰሱ በመስቀሉ አይታዥ ይፈወሱ ነበር። በዚህም ተአምራት እየተሳቡ ብዙዎች ክርስትያን ሆኑ። ይህንን ያዩ አይሁድ መስቀሉን ባንድ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቦታ ጣሉት። በየቀኑ የአካባቢው ደረ ቆሻሻ ስለሚጥልበት ያ ቦታ እንደ ጉብታ ሆነ። ምንም እንኳ ለማውጣት ባይችሉ ክርስቲያኖቹ ያን ቦታ ያውቁት ነበር። በኋላ ግን በጥጦስ ወረራ ክርስቲያኖች ኢየሩሳሌምን ጨርሰው ለቀው ስለወጡ የከተማዋ መልክ ፍጹም ስለተለወጠ መስቀሉ የተደፈነበት ቦታ ወዴት እንደሆነ ለማወቅ አልተቻለም። በዚህም ምክንያት ከሦስት መቶ ዓመት በላይ ተዳፍኖ ቆይቷል። በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የንጉሥ ቆስጠንጢኖስ እናት ንግሥት ወደ ኢየሩሳሌም ቀጠለች። እዚያም ደርሳ ጉብታ የሆነውን ሁሉ ብታስቆፍር መስቀሉ ያለበትን አላገኘችውም ሰውም ብትጠይቅ የሚያውቃት አላገኘችም። በመጨረሻ ግን የመስቀሉ መውጣት የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበርና አንድ አረጋዊ ሰው ኪርያኮስ የሚባል( ኪራኮስ - ደጎ) የዕሌኒን መቸገር አይቶ እንደሚከተለው ይመክራታል "አንቺም ከምረሽ ዕጣን አጭሰሽ በእሳትም አያይዢው የዕጣኑ ጢስ ወደላይ ወጥቶ ወደታች ሲመለስ አቅጣጫውን አይተሽ አስቆፍሪው በዚህ ምልክት ታገኝዋለሽ አላት፣ እሷም ያላትን ሁሉ አደረገች። "ዘዕጣን አንጸረ ሰገደ ጢስ ድኅ" የዕጣኑ ጢስ ወደ ላይ ወጥቶ ወደ ታች ሲመለስ መስቀሉ ያለበትን ቦታ በጣት ጠቅሶ እንደማሳየት ይህል አሳየ ያን ምልክት ይዛ አውጥታለች። "ብዕሌኒታ ዘደፈኑ አይሁድ ትመ ተረክበ ዕፀ መስቀል" (ድጓ) ይህን በዓል በመላው ዓለም ያሉ ክርስትያኖች ያከብሩታል። በሀገራችን እንደ ኢጋጣሚ ሆኖ የመስቀል በዓል ከጥቢ ወራት መግቢያ ጋር የተያያዘ ስለሆኑ የተለየ ድምቀት አለው።

በመስከረም 16 ባለገሩ በቀበሌው፥ የከተማው ሕዝብ ማዘጋጃ ቤት ባዘጋጀለት ቦታ ከየቤቱ ችቦውን ዕንጨቱን እያመጣ ይደምራል። ካህናቱም በደመራው ፊት ዙሪያ ጸሎት አድርሰው "መስቀል አብርሃ በከዋክብት አሰርገወ ሰማየ እምኩሉሰ ፀሐየ አርአየ" እያሉ ደመራውን ይዞራሉ። ቀጥሎም ሕዝቡ "ኢዮሃ አበባዬ መስከረም ጠባዬ" እያሉ በደመራው ዙሪያ ይጨፍራሉ። ግጥሙ የወራቱ እንጂ የመስቀል ባይሆንም ቁም ነገሩ የመስቀልን ክብር አይለቅም። ማታ ሕዝቡ በየደጁ ችቦውን እያበራ ደስታውን ሲገልጥ ያመሻል። በዐሥራ ሰባት ጧት ደመራው ይለኮሳል። አምድ እስኪሆን ድረስ ይቃጠላል ደመራው የተጸለየበትና የተባረከ ስለሆነ ሕዝቡ አመዱንና ተርኳሹን እየተሻማ ወደየ ቤቱ ይዞ ይሄዳል። ለሰውም ሆነ ለከብት መድኃኒት ነው።

በአዲስ አበባና ባካባቢው ግን ደመራውን የሚያቃጥሉት ወዲያው ጸሎቱ እንዳበቃ ነው። ከላይ እንደተገለጠው ይህ በዓል በሀገራችን በጥቢ ወራት ማለት አበቦች በሚፈነዱበት ወራት ስለሆነ ባንዳንድ አካባቢ የእንቁጣጣሽ በዓል ይባላል። እዚህ ላይ ዕንቁጣጣሽ የሚሉት ሕፃናቱ ልዩ ልዩ ቀለማት ያሏቸውን አበቦች ለቅመው አንድ ላይ በሰርዶ አስረው ከደመራው ዕለት ጀምረው ለጎረቤቶቻቸውና ላገኙት ሁሉ ይሰጣሉ። ሰዎችም የሀገር ትውፊት ነውና አበባውን እየተቀበሉ ገንዘብ ይሰጧቸዋል። ይህ ብቻ ሳይሆን በየቤቱ እየዞሩ ወንዶችም ሴቶችም ለየራሳቸው የሀገር ባህል ግጥም እየገጠሙ ይጨፍራሉ። ባለቤቶችም እንደ ሽልማት እያደረጉ ገንዘብና ሌላም ነገር ይሰጧቸዋል። አንድ ላይ አጠራቅመው ድግስ ደግሰው ይመገባሉ። በግራኝ ወረራ ብዙ ባህሎች ሲደመሰሱ የመስቀል በዓል ግን እንኳን በክርስቲያኖች ተገደው በሰለሙት ኢትዮጵያዊያን ዘንድ አልተረሳም። ለምሳሌ፦ በሀገራችን ብዙ እስላሞች የመስቀልን በዐል ከክርስቲያኑ ጋር እንደ ክርስቲያኑ አድርገው ያከብራሉ። እንግዲህ ከቀን በኋላ በወራሪ ኃይል ተገደው እስልምናን ቢቀበሉም ከአያት ከቅድመ አያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ክርስቲያናዊ ባህል

ሳያውቁ ያስብራታል ማለት ነው። ባህሉ የሰውን ምንጭ የሰውን የትመጣ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ መጽሐፍ ነውና። ከዚህም ጋር ብዙዎች እስላሞች ባንገታቸው መስቀል ያስራሉ። መስቀል የክርስቲያኖች ምልክት መሆኑን አያውቁትም። ይህም መሠረታቸው ክርስቲያን መሆኑን ያሳያል።

ለ/ ስብከት ሐ/ ብርሃን መ/ ኖላዊ፦ እንዚህ ሦስት በዓላት ከልደት በፊት የሚውሉ ሦስት እሑዶች ናቸው። ነቢያት ይወርዳል ይወለዳል ብለው በትንቢት ይጠባበቁት የነበረው መሲህ የዓለም ብርሃን የነፍሳት ጠባቂ ነው ለማለት በቤተ ክርስቲያናችን የመዝሙርና የጸሎት ሥርዓት ከልደት ቀደም ብሎ ያሉት ሦስት እሑዶች ስብከት ብርሃን ኖላዊ ተብለው ተሰይመዋል። አከባበራቸውም በቤተ ክርስቲያን ቀለም እንጂ ልዩ ሥርዓት የላቸውም።

ሠ/ ግዝረት፦ ይህ በዓል የሚውለው ጥር ስድስት ቀን ነው በሙሴ ሕግ ተጻፈ ሕጻን ሲወለድ በስምንት ቀኑ ይገረዛል። ይህን የሙሴን ሥርዓት ለምፈጸም ጌታ በተወለደ በስምንት ቀኑ ተገርዟል። የተወለደው ታኅሣሥ 29 ቀን ሲሆን ስምንተኛው ቀን የሚውለው በጥር ስድስት ቀን ነው። ይህ ቀን ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሲከበር ይኖራል።

ረ/ ልደተ ስምዖን፦ ይህም በዓል ጌታ በተወለደ በአርባ ቀኑ የሚከበር ነው። ጌታ ሥርዓተ ኦሪትን፤ ትንቢተ ነቢያትን ሊፈፅም እንጂ ሊያፈርስ ስላልመጣ ሕገ ኦሪትን ፈጽሟል። ለሙሴ ሕግን የሰጠ ሲሆን የሙሴን ሕግ ፈጽሟል። ከላይ እንዳየነው በስምንት ቀን ወደ ቤተ ግዝረት ገብቷል፤ አሁን ደግሞ በተጻፈው መሠረት የሙሴን ሕግ ለመፈጸም ሁለት ዋሊያ ወይም ሁለት የርግብ ጫጩቶች መሥዋዕት ሊያቀርቡ ወደ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ወሰዱት። በዚያም የእስራኤልን መጽናናት ይጠባበቅ የነበረ ስምዖን የሚባል ሰው ነበር። እሱም መሲሕን ሳያይ እንዳይሞት ከመንፈስ ቅዱስ ተረድቶት ነበር።

በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ መሠረት ይህ ስምዖን በ284 ከጌታ ልደት በፊት በበጥሊሞስ ዘመነ መንግሥት መጻሕፍተ ብሉያት ከዕብራይስጥ ወደ ጽርእ በተመለሱ ጊዜ ከመላሾቹ ከሰባው ሊቃውንት አንዱ እሱ ነበር። እንደ አጋጣሚም ለሱ የደረሰው ኢሳይያስ መጽሐፍ ነበር። "ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ" ከሚለው ሲደርስ ድንግል ትወልዳለች ብሎ መተርጎም ተቀባይ የማያገኝ አሳፋሪ ነገር መስሎት " ድንግል ትወልዳለች" የሚለውን ንባብ "ወለት ትፀንሳለች" ብሎ መለሰው። ተመልሶ እንደ ገና ቢያይ "ድንግል ትወልዳለች" የሚል ተጽፎ አገኘ ሁለተኛም ፍቆ "ወለት ትወልዳለች" ብሎ ጻፈ። እንደ ገና ቢያይ "ድንግል ትወልዳለች" የሚል ንባብ አየ። በሦስተኛው እፍቃለሁ ሲል የእግዚአብሔር መንፈስ ተገልጦ ተው አትፍቀው ይህን የተጠራጠርከውን ሳታየው አትሞትም አለው። ጌታ በእናቱ ዕቅፍ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ እሱም በእግዚአብሔር ፈቃድ መጥቶ እዚያ ተቀምጦ ነበር። ጌታን ከእመቤታችን ተቀብሎ ታቅፎ በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ ሁለት ከቁጥር 29 — 32 ያለውን ጸለየ።

ወደ ቤተ መቅደስ የገባበትና በስምዖን ዕቅፍ የታየበት ዕለት በቤተ ክርስቲያን ይከበራል ስምዖን ጌታን በታቀፈ ጊዜ ከእርጅናው መታደሱ ስለሚነገር በዓሉ የጌታ ሆኖ ሳለ ልደተ ስምዖን እያልን እንጠራዋለን። ሌሎቹ "የጌታ ወደ ቤተ መቅደስ መቅረብ" ይሉታል።

ሰ/ ቃና ዘገሊላ፦ ቃና በገሊላ ክፍል የምትገኝ ቀበሌ ናት በዚች ቀበሌ ውስጥ ጌታ ከሠርግ በዓል ላይ ተገኝቶ ነበር። ታሪኩን ከላይ በተጠቀሰው የወንጌል ምንባብ ውስጥ ይመለከቷል። የጌታ የመጀመሪያው ተአምር የተፈጸመበት ድርጊት ስለሆነ እናከብረዋለን ይህ በዓል የሚውለው በየካቲት 23 ቀን ነበር ጌታ ዕለቱን ተጠምቆ ዕለቱን ወደ ገዳመ ሬሐ ሔዷል። ከተመለሰ በኋላ በሦስተኛው ቀን ወደ ሠርግ ቤት ተጠርቶ በየካቲት 23 ውኃውን የወይን ጠጅ በማድረግ የመጀመሪያውን ተአምር አሳይቷል። አሁን ግን በዐሉና በዐልን ለማገናኘት ሲባል ጥር 12 ቀን የጥምቀት በዐል በዋለ በነጋው እናከብረዋለን።

ሸ/ ደብረ ዘይት፦ ደብረ ዘይት ወይራ የሞላበት ተራራ ማለት ነው። የሚገኘው በኢየሩሳሌም በስተምስራቅ ጥቂት ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ ነው። ጌታ ቀን መቅደስ ሲያስተምር ደቀመዛሙርቱ የምጽአቱን ጉዳይ አንሥተው ጠይቀውት ምልክቱን ገልጦ ነግሯቸዋል። የቤተ ክርስቲያናችን ሊቅ ቅዱስ ያሬድ የዓቢይ ጾምን አኩሌታ እሑድ የጌታ ዳግም ምጽአት መታሰቢያ አድርጎ መዝሙሩን በዳግም ምጽዓት ጽፏል። ስለዚህም ደብረ ዘይት ይባላል። በዚህ ዕለት ሕዝበ ክርስቲያኑ ያለውም የሌለውም እንጀራ ጋግሮ ጥሬ ቆልቶ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይወስድና ለነዳያን ይሰጣል። ለምን ይህን እንደሚያደርጉ ሲጠየቁ የሚሰጡት መልስ የሚከተለው ነው። የሞቱ ነፍሳት በዛሬው ዕለት ይሰበሰባሉ ዘመዳቸው የሆነ ጥሬ ወይም እንጀራ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዞ መጥቶ ለነዳያኑ የሰጠ እንደሆነ አይተው ደስ ብሏቸው ይመለሳሉ የሞተ ዘመድ እያለው አንድ ሰው በዚህ ዕለት የሚበላ ነገር ወደ ቤተ ክርስቲያን ወስዶ ካልመጸወተ የዘመዱ ነፍስ መጥታ የኔስ ወገኖች አልቀዋል ብላ ትመለሳለች" እያሉ ይተርካሉ። የአባባሉ ምሥጢር የዳግም ምጽአትን ነገር ይመለከታል።

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት

## The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order



ቀ/ የመጋቢት መስቀል ፦ ይህ በዐል የሚከበረው መጋቢት ዐሥር ቀን ነው። በንዳንድ የሀገራችን ሰዎች በንድ ስሌኔ በመስከረም ማስቆፈር ጀምራ መስቀሉ የወጣው መጋቢት ዐሥር ቀን ነው ይላሉ። ነገር ግን ይህን አተራረክ ለመቀበል በቂ ምስክር የለም በዓለምም ዙሪያ መስቀሉ የወጣበት ዕለት የሚከበረው መስከረም 17 ብቻ ነው ያም ሆኖ ይህ መጋቢት ዐሥር ቀን ከንኡሳት በዓላት ዘጠነኛው ነው። ዘጠኙን ዐበይት በዓላትና ዘጠኙን ንኡሳት በዓላት ከዚህ በመጠኑ በተገለጠው ለመረዳት ይቻላል።

ከነዚህ ሌላ የእመቤታችን በዓላት፦ ልደታ፣ በአታ፣ ፍልሰታና አስተርእዮ በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ ሲከበሩ የኖሩ ናቸው። ሌሎች በመቅድመ ተአምር የተጨመሩት 33ቱ በዓላት ማርያምና በየወሩ በ 21 የሚከበረው የእመቤታችን በዐል፣ በ29 የሚከበረው በዐለ እግዚእ፣ በ12 የሚከበረው የሚካኤል ሌሎችም በዓላት የተጨመሩት በዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ነው ይባላል። ከዚያም አያይዞ ሕዝቡ የቅዱሳንንና የመላእክትን በዐላት በየወሩ ማክበር ጀመረ። ለምሳሌ፦ ቅዱሳን መላእክት፣ ቅዱሳን ሰማዕታት ጻድቃንም በዓመት አንድ ጊዜ እንዲከበሩ በዓለም ዙሪያ ሁሉ ያለ ነው። በእኛ ግን በልዩ ልዩ ምክንያት ባለበት ሰበካ በትውልድ የመጣ ልማድ ሆኖ በቤተሰቡ ሁሉ ይከበራል። አያት ቅድመ አያቱ የጊዮርጊስን በዓል ያከብር እንደሆነ ልጁ የልጅ ልጁ ያያቱ ቃብት ነው እያለ በየወሩ ተቀምጦ ይውላል።

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን በቀኖናዋ ስፍራ ቆጥራ ያስተማረቻቸው የጌታ የእመቤታችን፣ የሐዋርያት፣ የመላእክትና የቅዱሳን በዓላት የተወሰኑ ሁነው ሳለ ሕዝቡ በግሉ ፈቃዱ ምክንያት እየፈጠረ ዛሬም በዓል ነው ነገም በዓል ነው ብሎ ተቀምጦ ቢውል ቤተ ክርስቲያንን አያስወቅሳትም። እንደ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም የዓመት ስንክሳር አላት። ይኸውም በየዓመቱ የሚከበረውን "ቅዱስ ጻድቅ" የሕይወት ታሪክና አሟሟት በዝርዝር የያዘ መዝገብ ነው። በዚሁ በስንክሳር መሠረት ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም በዓላትን ያከብራሉ። አሁን ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋት በዓላትን መቀነስ ወይም ጨርሶ መሰረዝ ሳይሆን የአከባበሩን ዓይነት ማስተካከል ነው። ወይም በግልጥ አነጋገር የበዐል ሥራ መፍጠር አለባት ሥራ ፈትቶ መዋል በዐል ማክበር አለመሆኑን ቀስ በቀስ ለምእመናኗ ማስረዳት አለባት፤ ምእመናን በዓሉንም አክብረው ሥራቸውንም ሠርተው ለመዋል ይችላሉና። የነበረውን በዐዋጅ መለወጥ ግን ትምህርቷን ያጣብቃል። በዐል ማክበር እንደ በሽተኛ ተኝቶ በመዋል አለመሆኑንም የቤተ ክርስቲያን አባቶች አስረድተዋል።ኢይደልዎሙ ለክርስቲያን ከመ የጽርዑ ተግባር በዕለተ ሰንበት ከመ አይሁድ አላ ይትገበሩ ከመ ክርስቲያን ወኢተተዐቀቡ ሰንበተ ከመ አይሁድ።

የዓመት በዓላት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚከበሩት በዑደት ነው። ለበዐሉ የተዘጋጀው መዝሙር እየተዘመረ ታቦቱ ከመንበሩ ተነሥቶ ቤተ ክርስቲያኑን ሦስት ጊዜ ከዞረ በኋላ ሥርዐተ ሕዝብ ይቀጥላል ይህ የሚሆነው ግን በሚቀደስባቸው ዕለታት ነው ውሎ ቅዳሴ ከሆነ ግን ታቦቱ ከዑደት ሲመለስ ጸሎተ ቅዳሴ ይጀመራል፤ ጸሎተ ቅዳሴው ሲፈጸም ሥርዐተ ሕዝብ ይሆናል።

ከነዚህ ከጠቀስናቸው በዐላት ሌላ በክርስትያን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን በመላ በብሔራዊ ደረጃ የሚከበር በዐል ቅዱስ ዮሐንስ (የዘመን መለወጫ) ነው። በኢትዮጵያኖች ሁልጊዜ አዲስ ዓመት የሚጀመረው በመስከረም ነው። የጥንት ሮማውያን አዲስ ዓመት የሚያከብሩ በመጋቢት ወር ነበር። መስከረም ለመጋቢት ሰባተኛ ወር ነው። "ሴፕቴምበር" ይሉታል" ሴፕቴም(septem) ሰባት ከሚለው ቃል የተወረሰ ነው። ከጢባርዮስ ቄሣር በኋላ የተነሡ አያሌ የሮም ነገሥታት በዚህ ወር ተሠይመውበታል። ይህንኑ ወር የእንድቅትዮን ወር ይሉታል (indieo) ከሚለው ላቲን ቃል የወጣ ነው።(indicto-onis) በአዋጅ መንገሪያ ትእዛዝ ማስተላለፊያ ውሳኔ መወሰኛ ማለት ነው "የበጀት ዓመት" እንዲሉ ለነገሥታት የሚሰጠው ግብር ለሃይማኖት አባቶች የሚቀርበው ግጽ በረከት ተሰብስቦ መፈጸም ያለበት በዚህ ወር ነው። በሀገራቸው የበጋው ወራት ፍጻሜ የክረምት ተጋባት በመስከረም ነውና "እንደ ሀገራችን ግንቦትና ሰኔ" ይህንኑ ወር በየአሥራ አምስት ዓመት የእንድቅትዮን በዓል እያሉ ያከብሩት ነበር።

ሕገ መንግሥት የሚታደስበት ውል የምፈርስበት የሚታደስበት በዓል ነው። ብሉይ ኪዳን ግን እሥራኤል ነጻ ከወጡበት ከመጋቢት ወር ጀምረው ቆጥረው በሰባተኛ ወር አዲስ ዓመት እንዲያከብሩ ከፈጣሪያቸው ታዝዋል። አዲሱን ዓመታቸውን በዚህ ወር የሚያከብሩ ከእግዚአብሔር ታዝዘው ስለሆነ ይህ ዐውደ ዓመት ለእሥራኤል ብሔራዊ ብቻ ሳይሆን ሃይማኖታዊ ድርጊቶች ይፈጽሙበታል።

ሊቀ ካህናቱ ኢፉዱን ለብሶ የሐር መጎናጸፊያን ይዞ የዓመቱን በዐላትና አጽዋማት ለሕዝቡ የሚያውጀው በዚህ ቀን ነው። በክርስትና ዓለም ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ይህንኑ የብሉይ ኪዳን ትእዛዝ ተቀብላ አዲስ ዓመት በመስከረም ወር መጀመሪያ እያከበረች ብዙ ዘመን ኑራለች። በኋላ ግን ከ1073 እስከ 1085 የነበረው የሮማ ፓፓ ጎርጎርዮስ ሰባተኛ የአዲስ ዓመት መጀመሪያ ከልደት እንዲያደርግ ለማድረግ በጥር

ወር ይሁን ብሎ ወሰነ። በዚህም ወሳኔ የካቶሊክ ግዛት የነበረው ምዕራቡ ዓለም በሙሉ ሲስማማ ምሥራቁ የክርስቲያን ዓለም ግን መስከረምን አለቀቀም። በፖለቲካና በንግድ ተጽዕኖ ምክንያት መንግሥታት በአቆጣጠር ወደ ምዕራብ ዓለም ቢሳቡም በመስከረም ነው። ለምሳሌ "ሩሲያ፣ ግሪክ፣ ሩማንያ" ሊሎችም። ይህንም የቤተክርስትያን አዲስ ዓመት ይሉታል።

በሀገራችን ግን ከጥንቱ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ነቁጥ ላይ ለወጥ የመንግሥቱም የቤተ ክርስቲያንም አዲስ ዓመት የሚጀመረው በመስከረም ነው። ይኸውም ለኢትዮጵያ ክብር ነው። ሁሉ በየጊዜው ባህሉን እየለዋወጠ ምንጩን አጥቶት ሲቸገር እሷ ለምስክርነት መገኘቷ ያስመሰግናልና። "መስከረም" ማለት ድሕረ ክረምት እንደ ማለት ነው በሀገራችን የክረምቱ የጨለማው ወራት ተፈጽሞ የበጋው የጥቢው ብርሃን የሚፈነጥቅበት ወር ነው። ስለዚህ በሀገራችን አዲሱ ዓመት ሁለት ዓይነት የአከባበር ጠባይ አለው። (ብሔራዊና ሃይማኖታዊ)። ነገር ግን አንዱ ከሌላው የተራቀቀ አይደለም። ብሔራዊ ያልሆነው ሕዝቡ ክርስትያኑም ሆነ ሌላው በብሔራዊ ስሜቱ የሀገር ልብስ ለብሶ ብሔራዊ ዘፈን አይዘፈን እርጾ ጠምቆ ሲባላ፣ ሲጠጣ፣ ሲገባበዝ፣ ሲጠያየቅ ይውላል። በሃይማኖታዊ ትውፊቱ ደግሞ ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄደ ለዚህ ያደረሰከኝ አምላኬ ተመስገን፣ የከርሞ ሰው በለኝ፣ ተርፎ ለሚቀረው ዕድሜ አትንፈገኝ ብሎ ፈጣሪውን ይለምናል። ካህናቱም በቤተ ክርስቲያን ለበዓሉ የሚገባውን ስብሐተ እግዚአብሔር ያደርሳሉ ዲያቆኑ መምህሩ ወይም መሪጌታው ካፖ ላንቃ ለብሶ መስቀሉን ይዞ በዓመቱ የሚውሉትን አጽዋማትና በዓላት ያውጃል፤ ባሕረ ሐሳብ ያወጣል። ቀጥሎም ፍሬያተ ምድር፦ ዕጣን ጧፍ፣ ዘቢብ፣ ሥንዴው፣ በምዕብ ወርቅ እየቀረበ ይባረካል።

በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት እያንዳንዱ ወንጌላዊ፦(ማቴዎስ ማርቆስ ሉቃስ ዮሐንስ) እያንዳንዱን የመጠሪያ ዓመት አለው ይህም በየአራተኛው ዓመት መጨረሻ ለመጀመሪያው ይደርሰዋል። (patron) ይሉታል ፈረንጆች ጠባቂ ማለት ነው። በኛም ይኸኑ ይመስላል። "ዮሐንስ አረሰ በማቴዎስ አፈሰ" እንዲሉ። የሕፃናቱ የአከባበር ትውፊት እንደ መስቀል ነው። ያንን ይመሰክሯል።

ከዚህ ሌላ ሕዝቡ ከጳጉሜን ጀምሮ እስከ መስከረም አንድ የወንዝ ውኃ ወዳለበት እየሄደ ጸበል ነው እያለ በሌሊት ይታጠባል። ይህም የቆየ ባህል ነው። አንዳንድ ሰዎች የአምልኮ ባዕድ ጠባይ ያለበት እየመሰላቸው ድርጊቱን ይነቅፋሉ። ነገር ግን የአምልኮ ባዕድ መርዝ እንዳይቀላቀልበት ሕዝቡን ማስተማር እንጂ በውኃ መጠመቁ ነውር አይደለም። ቤተ ክርስቲያን የምእመናንን ሕይወት ዘወትር በትምህርት ካልታቸው ማንኛውም መንፈሳዊ ተግባር በአምልኮ ባዕድ መበረዙ አይቀርምና። በመስቀልና በዘመን መለወጫ በዓል ዕለት ልዩ ልዩ ቀለማት ያላቸው ዶሮዎች ፍየሎችና በጎች ለዑቃቢ እየተባሉ ይታረዳሉ። ይህ ድርጊት ኢክርስቲያናዊ ስለሆነ ቤተ ክርስቲያን ትቃወማለች። እያንዳንዱ ሰው በራሱና በቤተሰቡ ልማድ የሚፈጠመው እንጂ ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት የተገኘ አይደለም። ስለ በዓላት በመጠኑ ይህ ነው፤ ከዚህ በማያያዝ ስለ አጽዋማትም በመጠኑ እንናገራለን።

ጾም(ጦም) ማለት ሰውነት ከሚፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ መከልከል መወሰን ማለት ነው። ወይም ለሰውነት የሚያምረውን የሚያስጎመኘውን ነገር መተው ማለት ነው። ጾም ከሃይማኖት ጋር ዘለዓለማዊ ዝምድና ስላለው ሃይማኖት ባለበት ቦታ ሁሉ ጾም አለ። ይልቁንም በብሉይ ኪዳን ጾም ከፍተኛ ቦታ አለው። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ከእግዚአብሔር ጋር በሚገናኙበት ወራት እህል ውኃ በፋቸው አይገባም ነበር። በኃጢአት በብዛት የታዘዘው የእግዚአብሔር መዓት የሚመለሰው ሕዝቡ በጾም ሲለምኑትና ሲማልዱት ነበር።

በሐዲስ ኪዳንም ጾም ሰው ሰራሽ ሕግ ሳይሆን ራሱ መድኃኒታችን በመዋዕለ ሥጋዌው የሥራ መጀመሪያ አድርጎ የሠራው ሕግ ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን በቁራኝነት አብሮ የሚኖር መንፈስ ርኩስ ሰይጣን እንኳ በጾም የሚወገድ መሆኑን መድኃኒታችን ተናግሯል። ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግሉ የታዘዙ ሐዋርያትም ከመንፈስ ቅዱስ በየጊዜው ትእዛዝ የሚቀበሉት በጾምና በጸሎት ላይ እንዳሉ ነበር። ለስብከተ ወንጌል የሚያገለግሉ ዲያቆናትን ቀሳውስት የሚሾሙትም በጾምና በጸሎት ነበር። እና ቆርኔሌዎስ ያሳበትን ያዩና ያገኙ በጾምና በጸሎት ፈጣሪያቸውን ማለዳው ነው። የጾም ሃይማኖታዊ ትርጉም ፈጣሪን መለመኛ ከኃጢአት ቁራኛ መላቀቂያ መሣሪያ ስለሆነ በጾም ወራት ላምሮት ለቅንጦት የሚበሉ ወይም ለመንፈሳዊ ኃይል ተቃራኒ የሆኑ ሥጋዊ ፍትወትን የሚያበረታቱ የአልኮል መጠጦችን ሥጋን ቅቤን፣ ወተትን የሚያበረታቱ የአልኮል መጠጦችን ሥጋን ቅቤን፣ ወተትን እንቁላልን ማራቅ ታዟል። ከመባልዕቱና ከሌላው ደስታ ጋር ባልና ሚስት በምንጣፍ በአልጋ አይገናኙም። ጾም በትምህርት ሐዋርያትን በሊቃውንትም ዘንድ ሲሰበክ ኖሯል። "ነዳያንን ለመመገብ የሚጾም ንዑድ ነው፣ ክቡር ነው" እንደ ተባለ፤ ጦመኛው ለምሳው ወይም ለራቱ ያሰውን ወጭ ነዳያንን እንዲረዳበት ለድኩማን ድርጅት ወይም በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ለሚገኙ ነዳያን መስጠት ጦምን የበለጠ ክርስቲያናዊ ያደርገዋል።

ጾም የታሪክ ደርጊቶችን እያስታወሱ ከኃጢአት ለመንጻት ስለራስ የታሰበውን ለነዳያን በመስጠት የሚጸም መሆኑን ተረድተናል። ጾም ለራስ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም፣ ለወዳጅ ብቻ ሳይሆን ለጠላትም ይጸማል። "ለሚያሳድዱህ ጸልይላቸው" እንደ ተባለ በደዌ ጻኛ በአልጋ ቁራኛ የተያዙትን፣ በስደትና በምርኮ ያሉትንም በጾም ወራት ማስታወስ መጸለይ ይገባል። በጾም ወራት ከመብልዕት መወሰን ብቻ ሳይሆን ዓይን ክፉ ከማየት፣ አንደበት ክፉ ከመናገር፣ የተቆጠበ እንደ ሆነ ጾሙን ክርስትያናዊ ያደርገዋል።

በሐዋርያዊት ቤተ ክርስትያን ባህልና ትውፊት ውስጥ ያሉ የምዕራብም ሆኑ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ከሐዋርያት የወረሱት የጾም ሕግና ሥርዓት አላቸው። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስትያናም ከመጀመሪያዎቹ አብያተ ክርስትያናት እንዷ ስለሆነች ፤ ይህ የጾም ሕግና ሥርዓት አላት። በሕጓም መሠረት ሰባት የጾም ወራት አሉ።

1. ዓቢይ ጾም
2. ጾመ ሐዋርያት
3. የፍልሰታ ጾም
4. የነቢያት ጾም
5. ገሃድ
6. የነነዌ ጾም
7. ዓርብና ረቡዕ ናቸው።

ሀ/ የመጀመሪያው ጾም፣ ዓቢይ ጾም ወይም ሁዳዴ ጌታ ከተጠመቀ በኋላ የጦመው የአርባ ቀን ጦም ነው። ምእመናን ጌታቸው ያደረገውን ምሳሌ ተከትለው ይጾሙታል። ዓቢይ ጾም ስምንት ሳምንት 56 ቀኖች አሉት። ከነዚህም ቀኖች ውስጥ ሰባት ቅዳሜ፣ ስምንት እሑድ ይገኛሉ ዐሥራ አምስት ቀን ማለት ነው። ከቀሪዎቹ እንጂ ከእህል ውኃ ስለማይጠመ የጦመ ወራት 40 ቀን ብቻ ነው። ይህም በጥንታዊቷ (primitive church) የነበረ ሥርዓት ነው። ለምሳሌ በ 384 ገደማ ከእስፓኝ ወደ ኢየሩሳሌም ቅዱሳት መካናትን ለመሳለም ረጅም ጉዞ የሄደችው(Egeria) ኤጌርያ የተባለችው ሴት የተሳላሚ ጉዞ በሚለው መጽሐፏ (peregrinatio ed loca Sancla) እንደጻፈችኛና የጥንት ክርስቲያኖችንም በዚህ አቆጣጠር ሲጠቀሙ ማየቷን ጽፋለች። የቆጵሮሱ ኤጲስ ቆጶስ ኤጲፋንዮስም በዚህ አቆጣጠር ይቆጥር ነበር። ሌሎች ደግሞ የመጀመሪያውንና የመጨረሻውን ሳምንት ለይተው ይቆጥራሉ። ለምሳሌ የመጀመሪያው ሳምንት ጾመ ሕርቃል ይባላል። ሕርቃል(ሄራቅሊዮስ) የቢዛንታይን ንጉሥ ነበር። ይህ ሳምንት በስሙ የተጠራበትም ምክንያት እንደሚከተለው ነው። በዘመኑ ፋርሶች ኢየሩሳሌምን ወረው የጌታን መስቀል ማርከው ወስደው ነበር። እሱ ወደ ፋርስ ዘምቶ መስቀሉን ከነሱ ነጥቆ ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሷል። በዚህ ምክንያት ክርስትያኖች ተደስተው ለስሙ መታሰቢያ ይሁን የጾም ሳምንት በቀኖና ውስጥ አስገቡት እየተባለ ይነገራል። ግሪኮች ግን ጾመ ሕርቃል የሚባለውን ነገር አያውቁም ግን በዚህ ሳምንት ከዕንቁላል ከአይብ ከዓሣ በቀር ሥጋ አይበላም ክልክል ነው። ጾም መሆኑም ይናገራሉ ከላይ የተጠቀሱትን መብልዕት መብላታቸውም በትድላ በደስታ የሰነበተ ሰውነት ወዲያው በጾም ሲደርቅ በሽታ እንዳያመጣባቸው ለጥንቃቄ ነው ይላሉ። የሳምንቱንም ስም "የአይብ ሳምንት ወይም ነጭ ጾም" ይሉታል።

የመጨረሻው ሳምንት ሕማማት ነው ሐዋርያት የጌታችንን መከራ ሞት እያሰቡ የጦሙት ነው ይላሉ። ያም ሆነ ይህ ሁሉም ከዐቢይ ጾም ጋር እንደ መርገፍና እንደ እጀታ ስለ ተያያዘ ከዐቢይ ጾም ይቆጠራል። ዐቢይ ጾም መባሉ የጌታ ጾም ስለሆነ ታላላቅ የሰይጣን ፈተናዎች (አርእስተ ኃጣውእ) ድል የተነሡበት ድል የሚነሡበት ጾም ስለሆነ ነው። በሕዝቡም ዘንድ ሁዳዴ ይባላል። ሁዳዴ ማለት የመንግሥት መሬት የመንግሥት ርስት ማለት ነው። የመንግሥት ሁዳዴ በሚታረስበት ጊዜ አዝመራው በሚሰበሰብበት ጊዜ ልጅ ዐዋቂ ሳይባል የመንግሥቱ ዜጋ ሁሉ ለሥራ ታጥቆ እንደሚነሣ ይህንንም የጌታ ጾም የጌታ ሁዳዴ የክርስቶስ ዜጎች የሆኑ ምእመናን ሁሉ ይጾሙታልና። የቤተ ክርስቲያናችንን መዝሙር ንባብን ከዜማው አስማምቶ አጠናቅሮ የተናገረው ኢትዮጵያዊ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በጾመ ድጓው በሁዳዴ ለሚገኙት እሑዶች ሁሉ የተለየ መዝሙር ስለ ሠራላቸው እያንዳንዱ እሑድ በመዝሙሩ ስም ይጠራል።

<u>የመጀመሪያው እሑድ</u>፦ ዘወረደ ይባላል። በመጽሐፍ መጀመሪያ አምላክ ከሰማይ መውረዱን ሰው መሆኑንና መስቀሉን ስለሚያወሳ ነው። ሙሴኒም ይሉታል። "ምናልባት ስለ ሙሴ ሕግና ጾመ ሙሴን ስለሚያነሣ ይሆናል።"
<u>ሁለተኛው እሁድ</u>፦ ቅድስት ይባላል። በተለይ ስለ ዕለተ ሰንበት ቅድስና ስለሚያወሳ ነው።
<u>ሦስተኛው እሑድ</u>፦ ምኩራብ ነው። በዚህ ሰንበት ጌታ በመዋዕለ ትምህርቱ ምኩራብ ገብቶ ማስተማሩ ይነገራል።

<u>አራተኛው እሑድ</u>፦ መጻጉዕ ነው። ድውያንን መፈወሱን ዕውራንን ማብራቱን የሚያነሣ መዝሙር ይዘመርበታል።
<u>አምስተኛው እሑድ</u>፦ ደብረ ዘይት ይባላል። በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ሆኖ ያስተማረው የዳግም ምጽዓትን ነገር የሚያስታውስ መዝሙር ይዘመራል።
<u>ሰባተኛው እሑድ</u>፦ ኒቆዲሞስ ነው። በሌሊት ወደጌታ እየመጣ ይማር የነበረው የኒቆዲሞስን ታሪክ የሚያስታውስ መዝሙር ይዘመርበታል።
<u>ስምንተኛው ሳምንት</u>፦ ሆሣዕና ነው። ጌታ በአህያ ውርንጭላ ሆኖ ሆሣዕና በአርያም እየተባለ ወደ ቤተ መቅደስ የገባበት ዕለት መታሰቢያ ነው። ከሠርክ ሆሣዕና እስከ ትንሣኤ ያለው ሰባት ቀን ሕማማት ይባላል በነዚህ ቀኖች ውስጥ ብዙ አዝማድ መባልዕት አይበሉም። ስግደት መጻሕፍትን ከድርሳናት ተውጣጥተው በግብረ ሕማማት ይነበባሉ። አዳም ከፈጣሪው ተጣልቶ የኖረውን የጨለማና የመከራን ዘመን በማስታወስ መንበረ ታቦቱ በጥቁር ልብስ ይሸፈናል። ልብሰ ተክህኖውም ጥቁር ነው።

<u>ኀሙስ፦ ጸሎተ ኀሙስ</u> ይባላል። ጌታ በፍጹም ትሕትና የደቀ መዛሙርቱን እግር ያጠበበትና ከነሱም ጋር ግብር ያገባበት ምሥጢረ ቁርባንን ያሳየበት ዕለት ነው። (ፈረንጆች) ዕለቱን (Maundy Thursday) ወይም (The Last Supper) ይሉታል። በዚህ ዕለት በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት የግብረ ሕማማቱ መጽሐፍ እንደሚያዘው ቅዳሴ ይቀደሳል። ከቅዳሴው ቀደም ብሎ ቄሱ ውኃውን በብርት አድርጎ በጌታ አምሳል የምእመናኑ ወደ የቤታቸው ሔደው ለበዓሉ የተዘጋጀውን ጻቦና ጉልባን ይበላሉ። ለትንሣኤ የተዘጋጀው ጠላ የሚቀመሰውም የዚያ ዕለት ነው። "ስለ ሕጽበተ እግር ካነሣን ዘንድ በሌሎች አኀት አብያተ ክርስቲያናት የሚታጠቡት በዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አምሳል ዐሥራ ሁለት ሰዎች ናቸው። በኛ ግን በቤተ ክርስቲያናችን ያሉት ሁሉ ሴትም ሆነ ወንድ ይታጠባሉ። ነገር ግን አሥራ ሁለቱን ምሳሌ ስለሚያቀርበው እኛም እንደነሱ ዐሥራ ሁለት ሰዎችን ብናጥብ የሐዋርያት ምሳሌ ነው።"

ከጸሎተ ኀሙስ በበነጋው ዐርብ የስቅለቱን መታሰቢያ ዕለት አጎበር ተሠርቶ ለስቅለቱ ነክ የሆኑ ምንባባት ሲነበቡ ይዋላል። ስግደቱም ለሰሞኑ ሁሉ የበለጠ ነው። ሠርክ ሲሆን እያንዳንዱ ምእመን ወደ ቄሱ እየቀረበ በሰሙነ ሕማማት ውስጥ የሠራውን ኃጢአት ይናዘዛል። ቄሱም በወይራ ቅጠል እየጠበጠበ ተጨማሪ ስግደት ይሰጠዋል። በዐሥራ ሁለት ሰዓት ሠርሆተ ሕዝብ ይሆናል። ሁለት ቀን የሚያከፍሉ እህል ውኃ ሳይቀምሱ ያድራሉ። የማያከፍሉ ግን ከሐሙስ የተረፈውን ጉልባንና ጻባ ይላኩታል።

ቅዳሜ ብሉይ ምእመናንና ካህናቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሰበሰባሉ የጧት ጸሎት ሲፈጸም "ግብረ ሰላም በመስቀል" ክርስቶስ በመስቀሉ ሰላምን መሠረተ ሰላምን ፈጠረ የምሥራች እየተባለ በቤተ ክርስቲያን ለተሰበሰበው ሁሉ ቄጤማ ይሰጣል። የምሥራች ምልክት ነው። ምእምናንም እየሰነጠቁ በራሳቸው ያስሩታል። ወደ ቤተ ክርስቲያን ላልመጡትም ካህናት በየሰበካቸው ልብሰ ተክህኖ ለብሰው መስቀልና ቃጭል ይዘው ቄጠማውን የምሥራች እያሉን ያድላሉ። ምእመናንም ቄጤማውን ተቀብለው ገንዘብ ያለው ገንዘብ ይሰጣል፤ ገንዘብ የሌለው ደግሞ ለጧፍ የሚሆን(ማግ) ልቃቂት ይሰጣሉ፤ "አንዳንዶች ደግሞ ከማለዳት እስከ ጸግም ትንሣኤ የሌትን ዕለታት ተከፋፍለው ይዘው ለሰበካቸው ካህናት ምግብ እያዘጋጁ ያመጣሉ። በጎንደርና በላስታ ሁሉም ባንድ ላይ በደጀ ሰላም ይመገባሉ። ወይንም ምእመኑ ካህናቱን በቤቱ ይጋብዛል። በአዲስ አበባ ግን ወደ የንስሐ አባታቸው ቤት ምግብ አዘጋጅ ይወስዳሉ(ያከፋይ) ይሉታል። በዚያ ግን ገብረ ሰላም ነው ይሚባለው"። ይህች ቅዳሜ "ሰንበት ዐባይ" ትባላለች። የፊተኛይቱ ቅዳሜ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ፈጥሮ ከሥራው ያረፈበት ዕለት እንደሆነች ይህች ደግሞ የሦስት ዓመት ከሦስት ወር የማዳን ሥራውን በመስቀል ላይ ፈጽሞ በከርሠ መቃብር ዐርፎ የዋለበት ዕለት ናት። ሁለተኛም ይህች ዕለት "ስዑር ቅዳሜ" ትባላለች። ስዑር መባሏ ባመት አንድ ቀን ስለምትጾም ነው። በባሳር ግን "ስዑር" ያለውን ይዘው ሰሞኑን ምንም ሳይሠሩ ሰንበቱም በዚህ ዕለት ይሠራሉ። "ቅዳሜ ሹር" እንዲሉ ቄጠማው የምሥራች ምልክት መሆኑ ከታሪክ ጋር የተያያዘ ነው ቄጠማው የምሥራች ምልክት መሆኑ ከታሪክ ጋር የተያያዘ ነው። ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚነግረን ዓለም በንፍር ውኃ በተጥለቀለቀ ጊዜ የኖህ መርከብ ማረፊያ አጥታ ስትንሳፈፍ የውኃውን ሁኔታ ለመረዳት ኖህ ርግብን መርከቡ መስኮት አሾልኮ ይለቃታል። እሷም ቄጠማ ባፏ ያዘለት ትመለስለች። ኖህ በዚህ ቄጠማ የውኃውን መድረቅ ተረድቶ ተደሰተ። መርከቡንም ለማሳረፍ ተዘጋጀ "ቄጠማ ለጥፋት ውኃ መድረቅ የምሥራች መንገሪያ እንደሆነ አሁንም በክርስቶስ ሞት ማየ ሥራይ ማየ ድምሳሴ ኃጢአት ሞተ ነፍስ ከሰው ልጆች ተወገደ የምሥራች ሲባባሉ ምእመናን ቄጤማ ይዘው ቄጤማ አስረው ይታያሉ። በዚህች ዕለት ባንዳንድ ቦታ ቅዳሴ ይቀደሳል። ባንዳንድ ቦታ አይቀደስም። የሚቀድሱት የሚሰጡት መልስ ከጥ የተፈጸመው ዐርብ ነው። ቅዳሴ መኖሩን የቤተ ክርስቲያናችን ሊቀ ቅዱስ ያሬድ በጻፈው የሰሌቱ "ክብር ይእቲ" ለማወቅ ይቻላል ይላሉ። አይቀድሱም የሚሉት ደግሞ ምንም እንኳ የምንቀበለው ሥጋ ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሐደው ቢሆንም በትንሣኤ ድል ማድረጉን ከማየታችን በፊት መሥዋዕት አንሰዋም፤ ያሬድ የሠራው "ክብር ይእቲ" ቀድሱ የሚል ትዕዛዝ የለውም ቅኔ ነው ይላሉ።

ያም ሆኖ ይህ ሁሉም ቢሆን በሃይማኖት ሥርዓት ልዩነትን ስለሚያመጣ የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ትራማይል እንዳይሆን አንድ ውሳኔ መወሰን የቅዱስ ሲኖዶስ ኃላፊነት ነው።

ለ/ ከዓቢይ ጾም ቀጥሎ ሁለተኛው የሐዋርያት ጾም ነው። የሰኔ ጾም ይባላል። ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ለሰበኩት ወንጌል ከመዋሐዳቸው በፊት የጾሙት ነው። ምእመናንም እነሱን ምሳሌ አድርገው ከጰራቅሊጦስ በኋላ ጀምረው ይጾሙታል። ይህ ጾም በሕዝቡ ዘንድ የወታደር ጾም ይባላል። ለሰበኩት ወንጌል ዘመቻ የተዘጋጁ ሐዋርያት በጾሙት ተምሳሌት በድሮ ዘመን ወታደሮች ለዘመቻ ሲነሡ ወይም ከዘመቻ ሲመለሱ በተሳቱ በተገደሉ ይቅር በለን ለማለት በቀኖና ይጾሙት ነበር ማለት ነው። ይህ ጾም በመባቻ ሐመር ከፍና ዝቅ ስለሚል የተወሰነ ቀን የለውም አንዳንድ ጊዜ ከአርባ ይበልጣል አንዳንድ ጊዜ ከሠላሳም ያንሳል።

ሐ/ ሦስተኛው ጾም የፍልሰታ ጾም ነው (ጾመ ማርያም ይባላል።) የፍልሰታ ጾም ከነሐሴ 1 እስከ 15 ያለው ነው። በቤተ ክርስቲያናችን እንደሚተረከው እመቤታችን ያረፈችው በጥር 21 ቀን ነው (በግምት በ50 ዓም ገደማ)። ሐዋርያት በድኗን ሊቀብሩ ወደ ጌቴ ሴማኒ ይዘዋት ሲሔዱ አይሁድ በተናቸው። በዚህ ጊዜ መላእክት የእመቤታችንን አስከሬን ወስደው በገነት አኑረውታል። በስምንተኛው ወር በነሐሴ አስከሬኗን እንደ ገና ከጌታ ተቀብለው በጸሎትና በምህላ ቀበሯት። በዚህ የቀብር ሥነ ሥርዓት ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ቶማስ አልነበረም። በተቀበረች በሦስተኛው ቀን እንደ ልጇዋ ትንሳኤ ተነስታ ስታርግ ቶማስ ከሀገረ ስብከቱ በደመና ተጭኖ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ ያገኛታል በዚህ ጊዜ ትንሳኤዋን ለሌሎች ሐዋርያት አይተው ለእሱ የቀረበት መስሎት ተናዶ (ፈቀደ ይደቅ እመደመናሁ) በፊት የልጅሽን ትንሳኤ ሳላይ ቀረሁ አሁን ደግሞ ያንቺን ትንሳኤ ሳላይ ቀርቼ ነው ብሎ ከደመናው ሊወረወር ቃጣው። በዚህ ጊዜ እመቤታችን ቶማስን አጽናናችው። ለምስክር እንዲሆነውም ሰበኗን ሰጥታው ዐረገች። ቶማስ ሐዋርያት ወዳሉበት ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ እመቤታችንን እኮ ቀበርናት ብለው ነገሩት። እሱም ዐውቆ ምሥጢሩን አይደረግም "ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር?" አላቸው። ለማሳየት መቃብር ሲከፍቱ አጧት። በዚህ ጊዜ እሱ እመቤታችንን ተነሥታ ዐርጋለች ብሎ ሁኔታውን ተረከላቸው። ለምስክር ይሆንህ ብላ የሰጠችውን ሰበኗንም አሳያቸው። ሰበኗን ለበረከት ቆርጠው ተከፋፍለው ወደ የሀገረ ስብከታቸው ተበታትነዋል። ባመቱ ትንሳኤሽን ቶማስ አይቶ እንዴት እኛ ይቅርብን ብለው ከነሐሴ አንድ ጀምረው ሱባኤ ገቡ። በነሐሴ 14 ቀን ቅዱስ በድን አድርጎ አምጥቶ ሰጥቷቸው ከቀበሯት በኋላ በ16 ተነስታለች። በዚህ ቀን ጌታ ቀድሶ እመቤታችንም በልጇዋ እጅ ቆርባለች።(ወተቀረበት በእደ ወልዳ)። (ሙሉውን ታሪክ በውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ይመለከቷል) ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን የእመቤታችንን በረከት ለማግኘት ትጾማለች። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የእመቤታችን በረከት ለማግኘት ትጾማለች። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይህን ጾም በተለይ ህጻናቱ ያከብሩታል። በዚህ የአስራ አምስት ቀን ጊዜ ውስጥ የማይጾምና የማይቆርብ ሕጻን የለም። ብዙ ሰዎች ቤታቸውን እየዘጉ በመቃብር ቤት ሱባኤ ገብተው በጾምና በጸሎት ይሰነብታሉ። በፍልሰታ ጾም ጊዜ በጠቅላላ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያለው ሁኔታ ሕዝቡ ልጅ ዐዋቂ ሳይል የሚያሳየው ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ ኢትዮጵያ ለእመቤታችን የፍቅር አገሯ በሆኗን ይመሰክራል። (በሌሎች የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ጾሙ የተከበረ ነው ታሪኩ ግን የእመቤታችን ዕረፍቷም ትንሣኤዋም በነሐሴ ወር ነው ይላሉ።)

መ/ አራተኛው ጾም ጾመ ነቢያት ይባላል። ከኅዳር 15 እስከ ታኅሣሥ 29 ቀን ያለው ነው። የጾሙ ወራት 43 ቀን ነው። "ልደት በታኅሣሥ 28 ቀን በሚውልበት በዘመነ ዮሐንስ ቅበላው ኅዳር 14 ነው ጾሙ በ15 ይጀምራል። በሌላው ግን ቅበላው በኅዳር 15 ነው ጾሙ በ16 ይጀምራል። ይህን ጾም የምንጾመው ነቢያት በየዘመናቸው ስለ መሲሕ መምጣት በናፍቆት ይጾሙ ይጸልዩ ስለነበር የእነርሱን አርአያ ተከትለን የክርስቶስን ልደት ከማክበራችን ቀደም ብለን ይህን ጾም እንድንጾም በሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ተሠርቷል። ይህ ጾም እንደ መጨረሻው በመማቢያውም ሊቃውንትን የሚያከራክር አንድ አቆጣጠር አለው።

ባጀማመሩ ላይ (በኅዳር) ምንፈቀ ኅዳር ስለሚል) አንዳንዶች ሊቃውንት የዚህ ጾም መጀመሪያው 16ኛው ቀን ነው ይኸውም በዘመነ ማቴዎስ - በማርቆስ - በሉቃስ ነው። በዘመነ ዮሐንስ ግን ልደት ወደ ኋላ መጥቶ በ 28 ቀን ስለሚውል በ 15 ጾም ይጀመራል ይላሉ። ግማሾች ደግሞ "አድልው ስጾም ነውና ባራቱም ዓመት ጾሙ 15ን አይለቅም ይላሉ። በፍቅር ከደረገት ግን የሚያከራክር የሚያጣላ አልነበረም።

ሠ/ አምስተኛው ጾም ግሃድ ነው፤ ገሃድ ማለት ለውጥ ልዋጭ ማለት ነው። ፍቹ ከዘይቤው አይገናኝም። ወይም እንደ ዘይቤው "ግልጥ" ማለት ነው፤ ይፋ ማለት ነው። በገሃድ እንዲሉ በግልጥ በይፋ ሲሉ ገሃድ የጥምቀት ብቻ ነው፤ ጥምቀት ረቡዕና ዓርብ በሚውልበት ጊዜ በኋላው የሚገኙት ማክሰኞና ሐሙስ የፍስክ ቀንነታቸው ወደ ጾምነት ተለውጦ ይጾማል። በነሱ ለውጥ ጥምቀት የሚውልባቸው የጾም ቀኖች

(ረቡዕና ዓርብ) የፍስክ ቀን ሁነው ይከበራሉና። ግድ የረቡዕና የዓርብ ሰሙን ነው ብለናል። ነገር ግን በሌሎችም ቀን ቢውል የጥምቀት ዋዜማ ይጾማል። ጥምቀት እሑድ ቢውል ቅዳሜ ጥሉላት አይበላም። ሰኞ ቢውል እሑድ ጥሉላት አይበላም። እህል ውኃ ግን አይጠምም። አንዳንዶች ግን ጥምቀት ሰኞ ቢውል ከቅዳሜና ከእሁድ አውጥተው ይጾማሉ(ቅዳሜ ስድስት ከእሁድ ሦስት)። ጥሉላት በሁለተኛው ቀኖች አይቀምሱም ይላሉ፤ ነገር ግን ገሃድ አንድ ስለሆነ (በላም ለሰለት ዋሕድ ዘበሙ ገሃድ) ሰኞ ቢውል ቅዳሜ ከጥሉላት መጾም በእንዲህ የገባ ልማድ ነው። ግድ ለጥምቀት ብቻ ነው፤ በልማድ ግን የልደትንም ዋዜማ ገሃድ እንለዋለን። ነገር ግን ልደት የሚውልባቸው ዓርብ ወይም ረቡዕ የፍስክ ቀን ሁነው እንዲከበሩ ቢታዘዝም በዋዜማው የሚገኙት ማክሰኞና ሐሙስም ከጾመ ነቢያት ጋር የተያያዙ ስለሆኑ በጾማቸው የግድ ነው። የማይጾሙ ሰዎች ግን መጨረሻውን ጾመ ነቢያት ሲበሉ ቆይተው ዋዜማውን ብቻ ገሃድ ነው ብለው ይጾማሉ።

ረ/ ስድስተኛው የነነዌ ጾም ነው።(ነይ ነይ) ይህ ጾም የሦስት ቀን ጾም ነው ሰኞ ማክሰኞ ረቡዕ። በመብጃ ሐመር ክፍና ገባ ስለሚል ቁጥሩ ከአጽዋማት ዐዋድያት ነው። አንድ ጊዜ በጥር አንድ ጊዜ በየካቲት ይሆናል። የቤተክርስቲያን አባቶች ይህን ጾም የወሰኑት የነነዌ ሰዎች በጾምና በጸሎት ከመዓት ከጥፋት እንደ ዳኑ ምእመናንም በጾምና በጸሎት ከፈጣሪያቸው ምሕረትና በረከት እንዲያገኙ በማሰብ ነው። (ስለ ሙሉ ታሪኩ ትንቢተ ዮናስን ይመለከቷል) (ብሉይ ኪዳን)

ሰ/ ሰባተኛውና የመጨረሻው ጾም ረቡዕና ዓርብ ነው። ረቡዕና ዓርብ ከትንሣኤ ጀምሮ እስከ ጰራቅሊጦስ እሁድ ድረስ ከሚገኙ ረቡዕና ዓርቦች በቀር ዓመት እስከ ዓመት ይጾማሉ። የሚጾሙበትም ምክንያት አላቸው።

<u>ሀ/ ረቡዕ፦</u> የአይሁድ ሸንጎ ወይም ሲንሃድሪየም ጌታን ዓርብ ዕለት ለመስቀል የመጨረሻ ውሳኔ ያስተላለፈው ረቡዕ ዕለት ነው ይባላል። በድኅነዓለም ሰለው ልጆች ሲል የተወሰነበትን የሞት ውሳኔ ሁልጊዜ በማስታወስ ክርስቲያኖች በዚህ ዕለት እንዲጾሙ ታዟል።

<u>ለ/ ዓርብ፦</u> እንደሚታወቀው ጌታ የተሰቀለበት የሞተበት ብዙ ፀዋን ሲቀበል የነበረው ተስፋ የተፈጸመበት ቅዱስ ዕለት ስለሆነ በቤተ ክርስቲያን በጾምና በጸሎት እንዲከበር ታዟል። እነዚህ አጽዋማት ከሰባት ዓመት በላይ ያለ ሁሉ እንዲጾማቸው ተወስኗል። ቅዳሴ የሚቀደሰውም ከእሑድና ከቅዳሜ በቀር በጾም ወራት ከሆነ በዘጠኝ ሰዓት ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ሌሎች ሳይገባቸው እንደሚሉት ቅዳሴና ቁርባን ጾም ያስገድፋል ተብሎ አይደለም። ጌታ ነፍሱን ከሥጋው የለየበትን ሰዓት ተከትሎ የተሠራ ሕግ ነው። የምንቀበለው ሥጋ ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሐደው ነው። ካሣ ተፈጽሞ ሥጋው ደሙ በይፋ የተሰጠን ጌታ ነፍሱ ከሥጋው ሲለይ ነውና። በጥንቱ ሥርዓት ግን ባሬም በገዳማትና በታላላቅ አድባራት ይህንን ሰዓት በማክበር ከእሑድ ቅዳሜና ከበዓለ ሃምሳ በቀር በሥዋዕት በሠርክ ነው።

ከዚህ በላይ ከብዙ በጥቂት የገለጥናቸው በይፋ በትእዛዝ የሚጾሙትን የሕግ አጽዋማት ነው። በግልና በፈቃድ የሚጾሙ ግን ለምሳሌ የጽጌ ጾም ሄሮድስ ሕፃና ግን ባሰፈኀ ጊዜ እመቤታችን ከልጅዋ ጋር ያደረገችውን የምድረ ግብጽ ስደት እያስታወሱ አያሌ መነኮሳትና ባሕታውያን ምእመናንም ይጾሙታል። ጾሙ የሚቆየው ለአርባ ቀኖች ከመስከረም 25 እስከ ህዳር 5 ነው። በጽጌ ወራት (በአበባ) ወራት ስለሚጾም እመቤታችንም በአበባ ስለምትመሰል ጾሙም "የጽጌ ጾም" ይባላል። ከዚህም ሌላ የዓመቱን መጨረሻ ወር ጳጉሜንን የሚጾሙ አሉ። ታሪኩ ዮዲት የእስራኤልን ጠላት ሆሎፎርኒስን ከመግደሏ በፊት የጾመችው ነው ይላሉ። ዮዲት ጠላቷን ለማጥፋት የቻለችው በጾምና በጸሎት ከፈጣሪዋ ኃይል አግኝታ ነው፤ እኛም ጠላታችንን ሰይጣንን ፈቃደ ሥጋን ድል ለማድረግ በጾም ከፈጣሪያችን ኃይልን መታጠቅ አለብን ሲሉ ምእመናን ኃጢአታቸውን ለንስሐ አባታቸው ተናግረው ተናዘው የሚጾሙት የቀኖና ጾም አለ። ይህን ሁሉ ያልነው ለማወቅ ያህል እንጂ በገዳም፣ በበረሃ ያሉ መነኮሳት ባሕታውያን ግን ከሕግ በላይ ዓመት እስከ ዓመት ይጾማሉ። ለጊዜው ስለ ጾም እዚህ ላይ ይበቃል።

ብጹእ አቡነ ጎርጎርዮስ በ1974 ካዘጋጁት
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ላይ የተወሰደ።